**<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።</u>**

## ትምህርት ሣልሳይ፦ ምዕራፍ ሁለት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

*በቤተክርስቲያን መጀመሪያ የራስን ታሪክና እምነት መረዳት ያስፈልጋል። አንድ ሕፃን ከሌሎች ዘመዶቹ ኹሉ በቅድሚያ የሚያውቀው ወላጅ እናቱን እንደኾነ ኹሉ በቤተክርስቲያንም ከኹሉ አስቀድማችኹ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችኹን እምነትና ሥርዓት የእመቤታችንን ክብርና አማላጅነት የቅዱሳን መላዕክትን የሰማዕታትንና የጻድቃንን ክብርና አማላጅነት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጠባዩን ሳይለቅ ማጥናት ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱስማ ማንኛ ውም የሚጠቅሰው መጽሐፍ ነው። ቤተ ክርስቲያናችሁን ካወቃችሁ በኋላ አኹን በደረጃው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ታጠናላችሁ።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?*

*<u>መልስ</u>፦ እግዚአብሔርን የምናውቅበት ምንጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መገለጫና መገኛ መንገዶች ያሳያል። የእግዚአብሔርን ሥራና ለሰው ያዘዘውን ትዕዛዝ ይነግረናል። እግዚአብሔር ለሰው የገባውን ቃል ኪዳን ያመለክተናል።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ ስንት ነው?*

*<u>መልስ፦</u> መጽሐፍ ቅዱስ ኹለት ክፍል ነው። አንዱ ብሉይ ኪዳን ይባላል። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ዕውን ለማድረግ መንገድ የሚያዘጋጅ ነው። ኹለተኛው አዲስ ኪዳን ነው። ለማዳን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን መፈጸሙን የሚናገር ነው።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስ መባሉ በምን ምክንያት ነው?*

*<u>መልስ</u>፦ የቅዱስ እግዚአብሔር ቃል ስለኾነ ነው። የሰው ሕይወት የሚቀደስበት መጽሐፍ ስለኾነ ነው።/ካልዕ ጢሞ. 3÷15/ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለኾነ እውነት ነው።/መዝ. 32÷4።/*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?*

*<u>መልስ</u>፦ ከእግዚአብሔር የተላኩ ቅዱሳን ሰዎች ጻፉት/ካል. ጴጥ. 1÷21። ኤር 1÷4-10።/*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ?*

*<u>መልስ</u>፦ ብሉይ ኪዳን ከ4400-400 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ነው። ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ከ45-98 ዓ.ም ከጌታ ልደት በኋላ ተጻፈ።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ በምን ቋንቋ ተጻፈ?*

*<u>መልስ</u>፦ ብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በአራማይክ ቋንቋ ተጻፈ በ284 ከጌታ ልደት በፊት በቶሎሜዎስ /በጥሊሞስ/ ዘመነ መንግስት ወደ ፅርዕ ቋንቋ ተመለሰ /ይህን ሥራ ያከናወኑት ሰባ ሰዎች ተመርጠው ስለኾነ የፅርዑ ብሉይ ኪዱን «ሴፕታጃንት» «የሰባው» እየተባለ ይጠራል / ይህንን የሰባወያን ሥራ ለማሻሻል በ366 ዓ.ም የሮማ ፓፓ የነበረው ዳማሱስ ሔሮኒሞስ « ጀሮም» የተባለውን ሮማዊ መናኝ ዕብራይስጥ ተምሮ ብሉይ ኪዳንን ከእብራይስጥ ወደ ላቲን እንዲመለስ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው እሱም 40 ዓመት ሙሉ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ዕብራይስጡን አጣርቶ ተምሮ ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ላቲን መልሷል።ይህም «ቩልጋታ»የሚባለው ነው። ሐዲስ ኪዳን የተጻፈው በዕብራይስጥ፣ በሮማይስጥና በፅርዕ ነው። ጲላጦስ በመስቀሉ ላይ እንደጻፈው ሦስቱም ቋንቋዎች በወቅቱ በኢየሩሳሌም የሚነገሩ ቋንቋዎች ነበሩና።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መባሉ ለምን ነው?*

*<u>መልስ፦</u> ብሉይ ኪዳን ብሉይ መባሉ አሮጌ ማለት አይደለም። የነበረው የፊተኛው ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቃል የማያረጅ የማይለወጥ ነውና ሐዲስ ኪዳን ማለትም ዘመን አመጣሽ ጊዜያዊ ማለት አይደለም። የቀደሙ ሰዎች የቀደመውን ሕግና ውል መጠበቅ ስላልቻሉ ውል ስለፈረሰ እግዚአብሔር እራሱ ውል ሰጭ ውል ተቀባይ ኾኖ ለሰው ልጅ የለገሰው የበለጠ ማለትነው።/ዮሐ 1÷16-17/ «ኪዳን» በብሉይ ዘመን እግዚአብሔርና ሰው የሚገናኙበት ውል  እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው መመሪያ ማለት ነው። /ኦሪት ዘፍ.17÷4። 24÷7-8። ነገሥት ካልዕ 23÷2። ኤር31÷31።/ በሐዲስ ኪዳን ግን ኪዳን የሚለው የእግዚአብሔር ልጅ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ያስተማረውን ትምህርትና በመስቀል ላይ ለዓለም መስዋዕት ኹኖ የሰጠውን ሥጋውና ደሙን ኪዳን ይለዋል።/ማቴ 26÷28። ሉቃ22÷20። ቀዳ.ቆሮ. 11÷26።ካል. ቆሮ 3÷6። ዕብ. 9÷15።/ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ዝመድና አላቸው። አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ታምቆ ኑሯል። ብሉይ ኪዳን ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ተተርጉሟል። /ሮሜ. 10÷4። ዘዳ. 18÷ 18። ኢሳ. 7÷14። 53÷2። ኤር 23÷5።ሕዝ.34÷23።/ አውግስጢኖስ  እንዳለው።/“NOVUM TESTAMENTUM IN VERERE LATET, VETUSTESTAMENTUM IN NOVE PATET.”/ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በሐዲስ ኪዳን ያልተጠቀሱ ስምንት ብቻ ናቸው። እነሱም፦ ዕዝራ፣ ነህምያ፣ አስቴር፣ መክብብ፣ መኃልይ፣ አብድዩ፣ ናሆም፣ ሶፎንያስ ናቸው።*

*<u>ጥያቄ</u>፦ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላሉ?*

*<u>መልስ</u>፦ አበው መጽሐፍ ቅዱስን በብዙ ምሣሌ መስለውታል። የመንፈስ ቅዱስ ምንጭ፣ የእግዚአብሔር መንግስት አደባባይ፣ የዘላለማዊነት ገነት ይሉታል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘወርቅም መጽሐፍ ቅዱስን በአክብሮት በቅንነትና በንስሐ ለሚያነበው ሰው እንደ ጥምቀት ነፍስን የሚያጥብና የሚያጸዳ*

ነው ብሏል:: አርጌንስም መጽሐፍ ቅዱስን በአክብሮትና በጥንቃቄ በመመርመር ማንበብ ዘወትር ሥጋውንና ደሙን እንደመቀበል ነው አለ:: ይኽንንም ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት ጌታ ለሐዋርያት ቀደም ሲል «ስለነገርኋችሁ ቃል እናንተም ንጹሐን ናችኹ» /ዮሐ. 13÷15::/ ያላቸውን ይዘው ነው:: ይኽም የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነሳ የሚጠራ ነው::

ጥያቄ:- የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስንት ናቸው?

መልስ:- የብሉይኪዳን ጸሐፊዎች ከ40 አይበልጡም:: የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ደግሞ 8 ናቸው:: እነሱም:- ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ይሁዳ ብቻ ናቸው::

ጥያቄ:- መጽሐፍ ቅዱስ በአኹኑ ጊዜ በስንት ቋንቋዎች ተጽፏል?

መልስ:- መጽሐፍ ቅዱስ በአኹኑ ጊዜ ከ1500 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተጽፏል::

ጥያቄ:- መጽሐፍ ቅዱስን እንድናጠና እግዚአብሔር አዟል ወይ?

መልስ:- አዎ! «እኔም ዛሬ የማዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤተህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሔድ፣ ስትተም፣ ስትነሳም፣ ተጫወተው፣ በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፣ በአይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይኹንልህ፣ በቤትህም መቃኖች፣ በደጃፍህም፣ በሮች ላይ ጻፈው ይላል::» /ዘዳ.6÷ 6-9:: ቀዳ ጢሞ.4÷16:: ቀዳ.ጴጥ 3÷15/

ጥያቄ:- ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ ይስማማሉ ወይ?

መልስ:- አዎ! ይስማማሉ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳ መንፈሳዊ ቢኾንም በውስጡ ለምድራዊ አገልግሎት የሚውሉ ፍልስፍና፣ ሥነ ምግባር፣ሥነ ጽሑፍ፣ ቅኔ፣ ቅመማ፣ ሃሳበ ከዋክብት የመሳሰሉት ኹሉ ይገኙበታል:: ፍጥረታት መጀመሪያ ከእግዚአብሔር መገኘታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ሰው ደግሞ እነዚህን ተረክቦ እግዚአብሔር በገለጠለት እውቀት/ሳይንስ /ለልዩ ልዩ ዘመናዊ ጥቅም ያውላቸዋል:: ሳይንቲስቱ የሚመራበትን አንጎል ቅሉ የሰጠው እግዚአብሔር ነው:: ክርስቲያኖች የሳይንስን መራቀቅ አይተው ሳይንስን እንደ ምትሃት እንዳያስመስሉ ሳይንቲስቶችም የምርመራቸውን ውጤት አይተው አማልክት ነን እንዳይሉ መጻሕፍት ይመክራሉ::/ቀዳ. ቆሮ 1÷29 - 31::/

ጥያቄ:- ባኹኑ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ችግር ምንድንነው?

መልስ:- ባለፈውም ኾነ ባኹኑ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ችግር ተመሳሳይ ነው:: ባነስተኛ ግምት መጽሐፍ ቅዱስ ሰባት አይነት ችግሮች ያጋጥሙታል:: እነሱም:-

1. እግዚአብሔር የለም የሚሉ/atheists /
2. እግዚአብሔር መኖሩንም አለመኖሩንም አናውቅም የሚሉ/agnostics /
3. እግዚአብሔርን አንፈልግም የሚሉ /Reprobates /
4. ፍጥረት ኹሉ እግዚአብሔር ነው የሚሉ/pantheists /
5. ራሳቸውን እንደ እግዚአብሔር የሚቆጥሩ /lgotists /
6. ኹሉም ሃይማኖት ልክ ነው የሚሉ/Universalists /
7. በወላጆቻቸው ዑቃቢ መንፈስ/አውሊያ/ የሚያምኑ/animists /:: እነዚህን የመሳሰሉት ኹሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ችግሮች ናቸው:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለእነዚህ ኹሉ መልስ እየሰጠ ነው::

ጥያቄ:- በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ወይ?

መልስ:- መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አይደለም:: የክርስትና ትውፊቶችም አሉን ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ማለት ከቃሉ ብቻ ሳይኾን ከቃልም ከመጽሐፍም፣ ከሥራም የተወረሱ ናቸው:: /ካል. ተሰሎንቄ 2÷15:: 3፣6::/

ጥያቄ:- መጽሐፍ ቅዱስን ለመፍታት መብት ያለው ማን ነው?

መልስ:- መጽሐፍ ቅዱስን ለመፍታት፣ ለመተርጎም ሙሉ መብት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ኦሪትን ለመተርጎም ባለ መብቱ ሙሴ እንደነበር:: ይህ ካልኾነ ግን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው ኹሉ በየእጁ የሚቆራርሰው ከኾነ ተንኮለኞችና ሽፋጮች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው ገብተው ቅዱሳን መጻሐፍትን እያጣመሙ ለጥፋታቸው እንዲስማማ ያደርጉታል:: ይህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ኹል ጊዜ የሚታይ የመናፍቃን አሻራ ነው:: /ካል. ጴጥ. 3÷16::/

ጥያቄ:- መጽሐፍ ቅዱስን የማጥኛ ዘዴ ቢነግሩኝ?
መልስ:- በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ለምትማሩ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥኛ ዘዴዎች ብዙዎች አሉ እነሱም:-

1- በስድ ንባብ ታሪኩን እንዳለ በማንበብ
2- ትርጓሜውን ማጥናት
3- በግጥም በመደርደር
4- በመዝሙር መልክ በመዘመር
5- በድራማ በማቅረብ::

በድራማ ማቅረብ ትምርትና ታሪክ ነክ የኾኑትን ክፍሎች እንጅ የተአምራት ክፍሎችን አይደለም:: በድንግልና መውለድ፣በድግልና መወለድ፣ በመስቀል ላይ መሰቀል፣ በአጠቃላይ በጌታና በእመቤታችን የተፈጸሙትን ኹኔታዎች በድራማ ማቅረብ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የማይታወቅ ነው:: ይህን ክፍል በድራማ ማቅረብ ከድፍረትም አልፎ ጽርፈት ነው:: በእርግጥ ከምዕራባውያን ተውሰው አንዳንዶች ሰዎች በቤታቸው ውስጥ የልደት ዕለት የቤተ ልሔምን ዋሻ አስመስለው ሰርተው ዛፍ መሰል እንጨቶችን ተክለው በረዶ የወረደበት ለማስመሰል ያንን በጥጥ ባዘቶ ሸፍነው ልዩ ልዩ ፕላስቲክ አሻንጉሊቶችን

በዋሻ ውስጥ አድርገው የኤሌክትሪክ መብራት ብልጭ ድርግም እያደረጉ የልደትን ምስል አቀማመጥ ጀምረዋል:: ይህ ታዲያ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አይታወቅም::

ጥያቄ :-የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስንት ናቸው?

መልስ:- በዕብራውያን አቆጣጠር 22 ናቸው:: እነሱም

ሀ. አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት:-

1. ዘፍጥረት፣ 2. ዘፀአት፣ 3.ዘሌዋውያን፣ 4.ዘኁልቁ፣ 5. ዘዳግም::

ለ. ስምንት መጽሐፍተ ነቢያት

| | |
|---|---|
| 1. ኢያሱ | 5. ኢሳይያስ |
| 2. መጻሕፍት /ሩት ጭምር/ | 6. ኤርምያስ |
| 3. ሁለቱ ሳሙኤል/እንደ አንድ | 7. ሕዝቅኤል |
| 4. ኹለቱ ነገሥት/አንደ አንድ/ | 8. አስራ ኹለቱ ደቂቀ ነብያት/እንደ አንድ |

*/አሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት አሞጽ፣ ሆሴዕ፣ ሚክያስ፣ ኢዮኤል፣ አብድዮ፣ ዮናስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስ ናቸው::/*

ሐ. አጊዮ ግራፍ የሚባሉ፣/ የመዝሙር፣ የቅዳሴ፣ የቅኔ ክፍሎች::/

| | | |
|---|---|---|
| 1. ኢዮብ | 2. መክብብ | 3. ኹለቱ ዜና መዋዕል/ እንደ አንድ |
| 4. ዳዊት | 5. መኃልይ | 6. ዕዝራ/ነህምያ ጭምር/ |
| 7. ምሳሌ ሰሎሞን | 8. ዳንኤል | 9. አስቴር |

እነዚህም 22 ይሆናሉ:: በዕብራውያን ፊደል አምሳል ሰቆቃውና ሩት ለየብቻ ቢቆጠሩ ግን 24 ይኾናሉ:: በራዕየ ዮሐንስ ያሉ የ24ቱ ካህናተ ሰማይ ምሣሌ ናቸው::

በኬልቄዶንያውያን አብያተ ክርስቲያናት 49 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሏቸው:: ከሉተር መነሳት ወዲህ ደግሞ የብሉይ ኪዳን መጻሐፍት ወደ 39 ዝቅ አሉ:: በአትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና የታወቁ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ::

| | |
|---|---|
| 1. ዘፍጥረት | 23. ሰቆቃው |
| 2. ዘፀአት | 24. ሕዝቅኤል |
| 3. ዘሌዋውያን | 25. ዳንኤል |
| 4. ዘኁልቁ | 26. ሆሴዕ |
| 5. ዘዳግም | 27. አሞፅ |
| 6. ኢያሱ | 28. ሚክያስ |
| 7. መሳፍንት | 29. ኢዮኤል |
| 8. ሩት | 30. አብድዮ |
| 9. የሳሙኤል መጻሕፍት /ኹለቱ እንደ አንድ/ | 31. ዮናስ |
| 10. ነገሥት /ኹለቱ እንደ አንድ | 32. ናሆም |
| 11. ዜና መዕል ቀዳማይ | 33. ዕንባቆም |
| 12. ዜና መዋዕል ካልዕ | 34. ሶፎንያስ |
| 13. ዕዝራ/ ዕዝራ ቀዳ፣ ዕዝራ ካልዕ:- ሱቱኤል | 35. ሐጌ |
| 14. ነህምያ | 36. ዘካርያስ |
| 15.አስቴር | 37.ሚልክያስ |
| 16. ኢዮብ | 38. ዮዲት |
| 17. መዝሙረ ዳዊት | 39. ጦቢት |
| 18. ምሳሌ ሰሎሞን | 40. ጥበበ ሰሎሞን |
| 19.መክብበ ሰሎሞን | 41.የመቃብያን መጻሕፍት/አንደኛ፣ ሁለተኛ/ |

20. መኃልየ ሰሎሞን
21.ኢሳይያስ
22. ኤርምያስ
42. መጽሐፈ መቃብያን 3ኛ. /ወልደ ኮርዮን/
43. ተግሣፀ ሰሎሞን
44. ሢራክ
45. ሔኖክ
46. ኩፋሌ ናቸው።

ጥያቄ፡- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስንት እንደኾኑ ቢነግሩኝ?

መልስ፡- በአንድ ጥራዝ የሚገኙ የሐዲስ ኪዳን መጻሐፍት 27 ናቸው። ይህን በአሃዝ ያስታወቀው የእስክንድርያው ሃያኛ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው። ይኸውም በ369 ዓ.ም በበዓለ ፋሲካ ባስተላለፈው መልዕክት ነው። በዘመኑ ብዙ አርዮሳውያንና መንፈቀ አርዮሳውያን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሚስማሟቸውን ንባቦች እየጨመሩ ስላስቸገሩ ለመጨረሻ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፎቿን ቁጥር እንድታውቅና እንድትጠነቀቅ አስረድቷታል። ይህ አሃዝ ከታወጀ ከአሥር ዓመት በኋላ በ379 ዓ.ም በካርቴጅ /ቅርጣግና/ በተደረገው ሲኖዶስ ይኸኑ የአትናቴዎስን ትምህርት በማጽደቅ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 መሆናቸውን አውጇል። ሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

1. የማቴዎስ ወንጌል /ከ60-68 ተጻፈ/
2. የማርቆስ ወንጌል /በ60 »/
3. የሉቃስ ወንጌል /በ61 »/
4. የዮሐንስ ወንጌል /በ98 »/
5. የሐዋርያት ሥራ /በ62 »/
6. የጳውሎስ መል. ወደ ሮሜ /በ58 »/
7 .የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮ. 1ኛ /በ56 »/
8. ወደ ቆሮንቶስ /ኹለተኛ/ በ57 »/
9 . ወደ ገላትያ /ከ48-49 »/
10. ወደ ኤፌሶን /በ60 »/
11. ወደ ፊልጵስዮስ /በ61 »/
12. ቆላስዮስ /በ59 »/
13.ቀዳ. ተሰሎንቄ /ከ52-53 »/
14.ካልዕ ተሰሎንቄ /በ 54 »/
15.ቀዳ. ጢሞቴዎስ /በ66 »/
16. ካልዕ ጢሞቴዎስ /በ66 »/
17.ቲቶ /በ66 »/
18. ፊልሞና /ከ59 - 61 »/
19. ዕብራውያን /በ69 »/
20. የጴጥሮስ መልዕክት 1ኛ /በ66 »/
21. የጴጥሮስ መልዕክት 2ኛ /በ66 »/
22. የዮሐንስ መልዕክት 1ኛ /በ98 »/
23. የዮሐንስ መልዕክት 2ኛ /በ98 »/
24. የዮሐንስ መልዕክት 3ኛ /በ98 »/
25. የያዕቆብ /ከ44- 45 »/
26. የይሁዳ /በ70 »/
27. የዮሐንስ ራዕይ /81 » /

ከነዚህ ጋር ባንድ ጥራዝ ባይሆኑም እኩል ተሰሚነት ያላቸው ስምንት መጻሕፍት አሉ። እነሱም፡-

1 ትዕዛዝ ሲኖዶስ /ረስጠአ ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ/ 71 ወይም 72 ቀኖና አለው።
2. ግጽው ሲኖዶስ /ረስጠብ ቀሌምንጦስ ዳግማዊ/ 56 ወይም 57 ቀኖና አለው።
3. አብጥሊስ ሲኖዶስ /ረሰጠጅ ቀሌምንጦስ ሣቲስ / 81 ወይም 83 ቀኖና አለው።
4. ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ /30 ቀኖና ወይም አንቀጽ አለው/
5. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
6. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ
7. ቀሌምንጦስ
8. ዲድስቅልያ ናቸው

ከሐዲስ ኪዳን ጋር እኩል ተሰሚነት ያላቸው እነዚህ ስምንት መጻሕፍት ከ27ቱ ጋር ሲደመሩ 35 ይኾናሉ። 35 እና 46 ሲደመሩ 81 ይኾናሉ።

እንግዲህ በቤተ ክርስቲያናችን የአቆጣጠር ቀኖና ለእምነት ለሥርዓትም የምንቀበላቸው መጻሕፍት 81 ናቸው።

**ይቆየን።**